# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org


*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ነሐሴ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

*ሰኔ እና ሰኞ ሲገጣጠሙ*

*ጌታ እና ሎሌ ሲሳሳሙ!*

"የት ይደርሳል ሲባልለት የነበረ ጥጃ፤ ቄራ መውረዱን እናውቃለን።" በአንፃሩ ደግሞ ፡ "የትም አትደርስም ሲባል የነበረው ወያኔ ፤ መዳረሻው ጎልጎታ መሆኑ ቀርቶ፤ ምኒክል ግቢ እንደሆነ ለማየት በቅተናል። የኢትዮጵያ ሕዝብም፤

"ዐይኔ ጉድ አየ ዕድሜየ ረዝሞ ፤
መከራው ሲመጣ ደግሞ ደጋግሞ፤
መጥተው ነገሩኝ የሀገሬን መርዶ፤
ዕባቡ ሄዶ ሲተካ ዘንዶ! " ብሎ ተቀኝቷል።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪካዊ የካቲት 1966 ( 1974) ዐብዮትን፤ መፈንዳት የኢትዮጵያ ሕዝብ አገዛዙን ለመጣል ሲጠቀምበት በደርግ አምባገናዊነት የተነሳ በተከተለው የአፈና፤ጭፍጨፋና ሽብር የተነሳ ሁኔታው ለ ተገንጣዮች አመቾቶ መገኘቱን የምናውቀው ነው። ደርግ ሀገር ወዳዱን ሀይል ሲፈጅ በሩን ለገንጣዮች በርግዶ ከፈተላቸው ።በመጨረሻም የራሱን መኮንኖችና ጄኔራሎች ሳይቀር ረሽኖና ጦሩን አዳክሞና ሀገርን አጋልጦ፤ሕዝብ ለወያኔና ሻዕቢያ አሳልፎ ሰጥቶ ወድቋል ።ቡከኑ ጀግና በሉኝ ባይ ኮለኔልም አሜሪካ ወደ አዘጋጀለት ስደት--ሕራሬ ዚምባብዌ=- የሀገሪቷን ገንዘብ ዘርፎ ፈርጥጧል።

ኢትዮጵያን ከኋላ -ቀርነት አውጥቶ፤ ታላቅና የበለፀገች ሀገር ለማድረግ ሲታገልና ሲሰዋ የነበረው ሀገር-ወዳዱና ሕዝብ- አፍቃሪው ተራማጅ ትውልድ በሩቁ ሲያስብና፤ ከድማስ ባሻገር ሲመለከት፤ ገንጣዮችና

አስገንጣዮቹ  እንደ ፍልፈል አፈር ሲርመሰመሱ ቆይተዋል። ሁኔታውንም አድፍጠው ጠበቁ።  "ብረቱ ሲግል  በመዶሻ ምታው!" ሆነና፤ ሀገራችንን ተባብረው አጠቋት!

መሃይሙ መንግሥቱ ሃይለማርያምም፤  ዕውነተኞቹን ኢትዮጵያውያን ጀግኖችና ሀገር ወዳዶች አንድ በአንድ ጨረሰላቸው። እነርሱም፤ ደስ አላቸው።  "ንንሃዶም ጠተፋፈኦም!" እርስ በእራሳቸው ተጠፋፉ! ብለው ተመጻደቁ ። ተደሰቱ። ወያኔና ሻእብያ ጮቤ ረገጡ። ዳይላ ዘለሉ። ሻዕብያ ለመገንጠል፤ ወያኔ ለማስገንጠል ተባረቡ። ኢትዮጵያዊው ኃይል እርስ- በዕርሱ ተላለቀ። መሃይሙ መንግሥቱና ተከታዮቹ የኢትዮጵያን ልጆች አረዷቸው።  ጀኔራል መኮንኖቹን፤ በመትረየስ  ረፈረፋቸው። ወጣቱንና ምሁራንን ጨፈጨፋቸው። ይህ ድርጊት ፤ ለኢትዮጵያ ጠላቶች ሥርግና ምላሽ ነበር። ለእኛ ግን መሪር ሃዘናችን ሆኖ ቀርቷል። አሁንም እንደ እግር እሳት ያቃጥለናል!

ሀዘናችንን ወደ ሃሴት፤ ቁጭታችንን ወደ መልካም ሥርዓት የምንለውጥበት ጊዜ ግን ሩቅ አይሆንም። ለሕዝባችን ዕድሜ ይስጠው።  እኛንም ያበርታን!  አንድነታችን አሰባስበን፤ ኃይላችን አጠንክረንና ሕዝባችንን አስተባብረን ሀገራችንን ከጥፋት አዘቅት እናወጣታለን። ይህ ደግሞ በቀቢፀ- ተስፋ ላይ የተመሠረተ ምኞት ሳይሆን ፤ መሥዋ ዕትን በሚጠይቅ ትግል ላይ የተመረኮዘ ዕምነት ነው።

በኢትዮጵያ ሕዝብ  ዐብዮት ስም የተፈፀመውን ይህንን ሀገራዊ ክኅደትና ወንጀል ለማስታወስ የተገደድነው፤  ዛሬም እንደ ትላንቱ በሀገራችን ላይ የሚፈፀመው በደል እየተደጋገመ  በመምጣቱ ነው። ወያኔ የሀገራችንን ሉዓላዊነትና ክብር ለአለቆቹ የእጅ መንሻ አድርጎታል። ባለፈው ሣምንት የአሜሪካው ፕሬዝደንት  የአዲስ አበባ ጉብኝት ምክንያት፤ የሆነውን ትዝብት ያጤኗል።

1ኛ. ለሦስት ቀናት ያህል፤ የሀገራችን ፀጥታና መንግሥታዊ ዕዝ፤ በአሜሪካ ፀጥታ ድርጅትና (ሲአይኤ) ወታደራዊ ቁጥጥር ስር እንዲሆን ተደርጓል። ከ800 መቶ በላይ የሆነ  የአሜሪካ የወታደርና የፀጥታ አባላት ከተማዋን ተቆጣጥረው ሰንብተዋል።

2ኛ. ቁጥራቸውን በውል ለመናገር የሚያስቸግር የጦር ሄሊኮፕተሮች  የአዲስ አበባን ሰማይ  ፀጥታና ሠላም ሲያውኩ ሰንብተዋል። አባቶቻቸው የኢጣሊያንን ወራሪ ኃይል መርተው ማምጣታቸው አንሶ፤ የነርሱ የልጅ- ልጆችም ከሰባ ዓመታት በኋላ ተመሳሰይ ድርጊት ቢፈጽሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይገርመውም።

3ኛ. ወያኔ፤ የአሜሪካ አሻንጉሊት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ ሀገራችንንም የዩናይትድ ስቴት ሀረግ- ሬሳ ገንደ-ጥር ( ባናና ሪፑብሊክ ) መሆኗን በአደባባይ አስመስክሯል። ባዕዳን ሲስሉ፤ መሃረብ ለማቀብል እንዴት እንደሚሽቀዳደሙ ለመታዘብ ችለናል። ይህን አሳፋሪ ተግባር፤ የትላንቱ ወዳጁ፤ የዛሬው ባላንጣው ሻዕቢያ እስካሁን እንዳላደረገው አስመስክሯል ። ቢያንስ ኤርትራን ከኢትዮጵያ በማስገንጠሉ፤ ሻዓቢያ "አርበኛ ነኝ" ብሎ ሲፎክር ሰምተናል።

በወርሃ ግንቦት፤ 1881 ዓም ገላባት ላይ መሥዋዕት የከፈለውን ዮሐንስ አራተኛ የኢትዮጵያን ንጉሥ አንገት ቆርጠው በመውሰድ፤ በሱዳን አምዱርማን ከተማ በሚገኘው አዳራሽ፤ ውስጥ የአንገቱን አፅም አስቀምጠውታል። ሙዚየሙን የሚጎበኘው ሰው ሁሉ፤ 5 የስዳን ፓውንድ እየከፈለ ያየዋል። የሰማዕቱን ዮሐንስ አንገት ሱዳኖች የገቢ ምንጭ አድርገውታል። ይህንን ማየት ለኛ አሳዛኝና አስቆጭ ነበር። የወያኔ መሪዎች ግን የሱዳኖቹን ርዳታ ለማግኘት ይሞዳሞዱ ነበር እንጅ ስለ ታሪካዊ ውርደት ደንታ እንዳልሰጣቸው እናውቃለን።

"ጅብን ሲወጉ፤ በአህያ ይጠጉ" እንደሚባለው፤ ወያኔዎቹ ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ለመጉዳት የሚፈልጉትን መጠጊያ/ መከለያ አያጡም። ትላንት የሶማሊውን መሪ ሲያድ ባሬን ተጠግተው ኢትዮጵያን የሚወጉበትን መሳሪያ እንዳገኙ እራሳቸውም አልካዱትም። ዛሬም በሥልጣን ለመሰንበት፤ ለአሜሪካን ጥገኝነት ቢያጉበድዱ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቶ አይደነቅም። ይህንን ለማረጋገጥ በአሁኑ ሰዓት የአዲስ አበባን ነዋሪ ብቻ መጠየቅ በቂ ነው። በተለይ ባራክ ኦባማ አዲስ አበባን ጎብኝተው በኋላ ሕዝቡ ምን እንደሚል ማዳመጡ ብቻ ይበቃል። ይህን መረዳት አቅቷቸው ግን ያወቁ የተራቀቁ መስሏቸው የኦባማ ጉብኝትም ሆነ ንግግር ሕዝብን አስደሰተ የሚሉ ማፈሪያዎች ሲለፍፉ መስማቱ ደግሞ ሌላ ምጸት ሆኖብናል።

4ኛ. የወያኔ ሰዎች ዛሬ ይህንን አሳፋሪ ደርጊት መፈፀማቸው ለኛ አዲስ ሊሆንብን ግን አይችልም። ኢሕአፓ፤ ሱዳኖች የኢትዮጵያን ወሰን ጥሰው በመግባት ዛፍ እየቆረጡ ሊወስዱ ሲሞክሩ ተዋግቶ አስጥሎ ወደመጡበት መልሷቸዋል። በቋራ በኩል በነፍሶ ገበያ አካባቢ ገብተው ሲሞክሩም አግዷቸዋል።. ይህም በሱዳን መሪዎች ጥርስ አስገብቶታል። ወያኔዎቹ፤ የሀገርን ታሪክና ሉዓላዊነት ከደውና አዋርደው ከጠላት ጋር ተመሳጥረው ለሥልጣን መወጣጫ ተጠቅመውበታል። አሁንም ቢሆን በሥልጣን ለመቆየት የሚጠቅማቸው ሆኖ ካገኙት፤ ለሰው መንግሥት ቀርቶ፤ ለመንግሥት-ሳጥናኤል እንደሚሰግዱ አንጠራጠርም። ጌታ የመለዋወጥ ልምዱ ስለ አላቸው፤ ዛሬ ለአሜሪካ የሚሰጡትን አገልጋይነት አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት፤ ነገ ለቻይናዎቹ ሙሉ በሙሉ እንደሚያስረክቡ መጠራጠር አይቻልም።

4ኛ. "የሰኔና የሰኞን መገጣጠም በሚገባ ወያኔ ተጠቅሞበታል" እያሉ፤ የጥቅመኝነት ባኅሪ በማሳየት የሚሞዳሞዱ ክፍሎች እንዳሉ እናውቃለን። ለወያኔ የሚጥመውን ሙዚቃ እያሰሙ፤ መልካቸውን እንደ እስስት በመለዋወጥ እየቀረቡ ሹመት- ሽልማት፤ ሀብት ንብረት ፤ ሥልጣንና ጥቅም ለማግኘት የሚሯሯጡትን ታዝበናል። ዓላማን ሽጦ፤ ዕምነትን አጉድሎ፤ ህሊናን አዋርዶ፤ ሀገርንና ሕዝብን ክዶ፤ ከባለ ጊዜ ጋር ተመሳስሎ ማደር፤ "የሠለጠነ ፖለቲካ ነው" ይሉታል።

በዓላማቸው ፀንተው የሚታግሉትን ኃይሎች፤ ደግሞ "ወይ አይበሉ፤ ወይ አያስበሉ" ይሏቸዋል። ለእነርሱ፤ በልቶ ከሚያጎርስ፤ ውራጅ ከሚያለብስ፤ ደግሶ ከሚያስቀላውጥ፤ በጭፈራ ከሚያስረግጥ ጫማ ስር ወድቆ ማገልገልን የመጨረሻ ግብ አድርገው ይቆጥሩታል። በሰሞኑ ጉብኝታቸው፤ ፕሬዝደንት ኦባማ፤ "የግንቦቱ፤ የወያኔ ምርጫ፤ ዴሞክራሲያዊ ነበር" አሉ ስለተባለ። የወያኔ አጫፋሪዎች በደስታ እንደፈነደቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቱን ያህል እንደታዘባቸው አላወቁትም። ሕዝቡ ግን በኦባማ ንግግር አንጀቱ አርሯል። እኛም የሕዝባችን ንዴት ተካፋዮች ሆነናል።

ከላይ የተመዘገቡት ሁኔታዎች፤ ኖሩም አልኖሩ፤ ተደጋገሙም ተከለሱ፤ የሀገራችንን መሠረታዊ / ሀገራዊ ዕውነታን ሊለውጡ ከቶ አይችሉም ። ይህንን ስንል የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ማለትም፤

1ኛ. የጌታና ሎሌ ቁርኝነት፤ በመግዛትና በመገዛት፤ እንዲሁ በሀገሮች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት በጊዚያዊ ጥቅምና በእከክልኝ - ልከክልህ ላይ ያተኮረ ስለሚሆን፤ ፍቅሩ፤ ዕፍ- ሲሉት ጭልጥ ሆኖ ይቀራል። ወትሮውን ቢሆን፤ በጊዚያዊ ጥቅም ላይ ብቻ ያተኮረ ግንኙነት ፤ እንደ ዕንግዳ ደራሽ፤ እንደ ወሃ ፈሳሽ ሆኖ ይጠፋል። ዘለዓለማዊቷ ሀገራችን ግን መኖሯን ትቀጥላለች ። ሕዝቧም፤ እየኖረ ይኖራል እንጅ፤ እየሞተ አይኖርም።

2ኛ. እስካሁን በሀገሪቱ የተፈራረቁ ገዥዎች በሥልጣናቸው ሊቆዩ ይቻሉት ባዕዳን ኃይሎችን በመተማመን ስለነበር፤ ባዕዳኑ ሲከዷቸው፤ እንደ ባቢሎን ግንብ ተፈረካክሰው ይወድማሉ ። የደርግንና የሶቬየቶችን መንኮታኮት ያጤኗል። የነ ባራክ ኦባማና የነወያኔ ዝምድናና ፍቅርም ከዚህ ታሪካዊ ሃቅ ሂደት ሊያመልጥ አይችልም። አሜሪካኖች፤ ወያኔን ከተጠቀሙበትት በኋላ፤ "አፍንጫህን ላስ" እንደሚሉት ያለፉት ተግባራቸው ያረጋግጣል። የኢራኑን ንጉሠ ነገሥት ሻኽ በሃላቢን፤ የኮንጎውን ሞቡቱን፤ የግብፁን ፕሬዝዳንት ሆስኒ ሙባርክን አስታውሶ ማለፍ ይበቃል።

ይህ ስለተባለ ግን፤ ምዕራባውያኑ፤  ኢትዮጵያን፤ እንዲሁ በቀላሉ ጠብ- እርግፍ አድርገው ይተዋታል ማለት አይደለም። የወያኔን ያህል ታማኝ አገልጋይ ሊያገኙ  የሚችሉበት  ሁኔታ ላያጋጥማቸው ይችል ይሆናል ቢባልም፤ ሌሎች የሚጋለቡ ፈረሶችን ግን  ሊያጡ  አይችሉም።

 አሁንም ለዚህ ዝግጅት  ሊጡ እየተቦካና ድፍድፉ እየተጠነሰሰ  መሆኑ፤ የሀገሪቱን ፖለቲካ በአንክሮ የሚያስተውሉ  ባለሙያዎች በቅርብ  ዕርቀት ይከታተሉታል።  ለወር ተራ የሚጠባበቁትን  ማሰልጠን ደግሞ አሜሪካኖች የሚቸግራቸው ተግባር  አይሆንም።

እዚህ ላይ፤  አንድ የማይታበል ሃቅ ጠቅሶ ማለፍ አስፈላጊ መሆኑ አይቀርም።  ሀገሩን  ወዳድና ሕዝቡን አፍቃሪ የሆነ መሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን እንዲይዝ  ምዕራባውያን  የሚያስደስታቸው  አለመሆኑ ነው።  ይህንን  ዘዴያቸውን  የተረዳ  ክፍል፤ የም ዕራባውያኑን   ድጋፍና  ትብበር  ለማግኘት ብሎ፤ ያለጥርጥር፤  መርኅን  ሽጦ  መቅረብ  አለበት። ይህ    ደግሞ የ "ሥልጡን ፖለቲካ"  ዕውቀትና ጥበብ   ይባልለታል።  ወያኔም ትላንት፤ የምዕራቡን ደጋፍ ለማግኘት ሲል፤ ከአልባንያ ሶሻሊዝም ጀንበሯ ሳትጠልቅ፤  ወደ ምዕራቡ ከፒታሊዝም ተለወጥኩ ብሎ  ቆዳውን ሽልቅቆ መስገዱን፤  የኢትዮጵያ ሕዝብ ታዝቧል።

ሥልጣን ለመያዝ የሚቋምጡ  ሁሉ፤ መርኅ፤ ኢትዮጵያዊ ሰብዕና፤  የሞራል ልዕልና፤  የአቋም ጥንካሬ፤ ለታሪክና ሕዝብ ተጠያቂነት፤ ለትውልድ ኃላፊነት፤ ለኅሊና ተግዥነት  ወዘተ... የሚባሉ  የሰው ልጅ ክብር መለኪያዎች አይኖራቸውም።  እነኝህ  ጉዳዮች፤ ለነእርሱ  የሞራል ስብከት፤  ጊዜው ያለፈባቸውና ወደ  ሥልጣን  ለመውጣት  እንቅፋቶች  እንደሆኑ  ይቆጥሯቸዋል።      እንደዚህ   ዓይነት   ሰዎች፤ የመጀመሪያና  መጨረሻ  ጉጉታቸው፤  በሆነው  መንገድ  ሥልጣን  መጨበጥ   ብቻ  ነው።  ወያኔዎቹም ይህንን አድርገዋል። ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ግን ሁሉም ስለሚያውቀው ያንን ለመዘርዘር አንጨነቅም።

 ሀገራችን  ከገባችበት  አዘቅት  ለማውጥት  ግን  እንጨነቃለን። ቁጭቱና ጭንቀቱ፤ ዕንቅልፍ   የሚነሳ ሆኖብናል።  ቁጭቱና ጭንቀቱ  የውስጣችን  ኃይል ሰጭ  ሆኖ፤  ትግላችንን እንድናጠናክር ረድቶናል። ፍትህ-  ርትዕ  ነግሦ፤  የኢትዮጵያ  ሕዝብ   የራሱን  ሥርዓተ    መንግሥት    እስኪመሰርት  ድረስ የምንታገለውም  በዚህ ኃይልና ቁጭት ነው።  "ጭራሽ አለመንበርከክክ!" የትግላችን ሰንደቅና ቋሚ መርኅ ነው!

3ኛ.  ቁጥሩ  ወደ  95 ሚሊዮን የሚገመተውን  ሕዝብ፤  በአንድ  ብሄር ስም  በተደራጀ  አንድ አምባገነን ፓርቲ  ታፍኖ  በመግዛት ብዙ ጊዜ የሚቆይ አይሆንም። ጭቆናው ሞልቶ ሲገነፍል  የሚያቆመው ኃይል

አይይኖርም። ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ፤ የአካባቢውን ጸጥታና መረጋጋት ቆሞ ከማየት የበለጠ ምርጫ ከማይገኝበት ደረጃ ይደረሳል። በሦርያ ፤ በየመንና በኢራቅ-ኢራን እንዲሁም በሶማሊያ እንዳለው ሁኔታ የሚከሰትበት አጋጣሚ ሊፈጠርም ይችላል። ሁኔታውን ልክ እንደ ገነፈለ ብረድስት ሾሮ የታንኒካ ቀዝቃዛ ውሃ ቢከልሱበት የሚቅዘቅዝ አይሆንም። የ95 ሚሊዮን ሕዝብ እሳተ- ገሞራ ማዳፈን አይቻልም። ፍንዳታው በስልት፤በግረትና በበቂ ድርጅት ከተያዘ ግን ትርምስምስና ፍጅት ሳይሆን ሀገራዊ ለውጥ ሊከሰት የሚችልበት ነው። ወያኔ ከወደቀ ኢትዮጵያ ያበቃለታል የሚሉ ችንፈተኞችና ጨለምተኞ ጎራቸው ከሕዝብ አለመሆኑ ግልጽ ከመሆኑ በላይ የፈሩት እንዳይደርስ አምርሮ መታገል ነው እንጂ ሙሾ በመደርደር ወያኔ በጫንቃችን ላይ ተቀምጦ ይባጅ ማለት አሳፋሪ ነው።

መላውን ዓለም ያጥለቀለቀው የስደተኛው ጎርፍ ሌላ ተጨማሪ ማዕበል ለማስተናገድ፤ ዓለም ዝግጅቱም ፈቃደኝነትም ሊኖረው አይችልም። መፃኢውን የኢትዮጵያ ዕሳት-ገሞራ ከወዲሁ ለማብረድ ዛሬ በጊዜው ብልሃት ካልተበጀለት፤ እሳቱን የቆሰቆሱት ብቻ ሳይሆኑ፤ ዳር ቆሞ የተመለከተው ሳይቀር፤ እንደሚርመጠመጥ ሊረዳው ይገባል። ምእራብያኑ ይህንን ክስተት ሳይገነዘቡት ይቀራሉ አይባልም። ለኢትዮጵያ በጎ ከመመኘት ሳይሆን፤ ለራሳቸው ሲሉ ብቻ ሁኔታ ከቁጥጥራቸው ውጭ ከመውጣቱ በፊት ሊያስቡበት ይገባል ብለው የሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች በርካታ እየሆኑ መጥተዋል።

4ኛ. ወያኔዎቹና አዲስ ነፍጠኞች ሆነናል የሚሉትም ከፍሎች ያላቸው ዓላማ አንድ ብቻ ነው። ወያኔዎቹ፤ በሥልጣናቸው ለመቆየት ሲሉ ለአለቆቻቸው የበለጠ ታማኝነታቸውን ለመግለፅ መጣጣር ሲሆን፤ አዲስ የሥልጣን ተስፈኞች ደግሞ፤ ከወኔ የበለጠ ታማኝ ለመሆን መጣጠር ነው። ሁለቱም ለሕዝቡ ጉዳትና ጥፋት ደንታ ሊኖራቸው አይችልም። የጋራ ጌቶቻቸውን ለማስደሰት ሲሉ በሚያደርጉት እኔ እበልጥ- እኔ እበልጥ ፉክክር በመሀል የሚጎዳው ንፁሃኑ ሕዝብ ለመሆኑ ያለፈው ታሪካችን ግሉህ ማስረጃ ይሆናል። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ጆርጅ ቡሽ፤ ወያኔን አዲስ አበባ እንዲገባ በር እንደከፈቱለት ሁሉ ባራክ አባማ፤ ወያኔን ልንተካ ነን ለሚሉ አፍቅሮ አሜሪካ ላላቸው ሀይሎች ቡራኬያቸውን እንደሚለግሱላቸው ማን ይጠራጠራል? ነባሩ ጌታ እንዳለ ሆኖ፤ አገልጋዮቹ የማይለዋወጡበትስ ምን ምክንያት ሊኖር ይችላል?

"ጉልቻው ተለውጦ፤ ወጡ ካልጣፈጠ፤

አዲስ አሽከር እንጅ ምንስ ተለወጠ? "

ብሏል የኢትዮጵያ ሕዝብ !

ይህንን ተጨባጭ ሁኔታ በግምት ማስገበት የሃቀኛ ታጋዮችና ለሥልጣን የማይቋምጡ ሀገር ወዳድ ወገኖች ተግባርና ኃላፊነት ነው ብለን እናምናለን። "ውሃ ውሃው ሂያጂ አለቱ ቀሪ" መሆኑን አለመርሳት ብልህነት ከመሆኑ በላይ ፤ ሀገርንም ከጥፋት ለማዳን የሚያስችል ግንዛቤ ነው። በራሱ ከሚተማመን ህዝብ አብራክና ማህፀን የተገኘን ትውልድ፤ በሰኔና- ሰኞ ግጥምጥሞሽ ፖሊቲካ ጨዋታ ማታለል አይቻልም። ይልቁንም፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች እያጤነ ይታገላል።

1ኛ. የትግራይን ሕዝብ ሽፋን አድርጎ የመጣው ወያኔ፤ ማንንም የሚወክል ተግባርና ባኅርይ የለውም። በቅርጽ ተሰቦ፤ በስሜት ተውጦ ወያኔን ሲደግፍ የነበረው ሁሉ በጣት ከሚቆጠሩት በስተቀር ፤ ፀፀቱ እንደ እግር ዕሳት እያቃጠለው መሆኑን ተገንዝበናል። ወያኔ፤ ጊዜ ሲከዳው፤ ይህ ክፍል፤ ውሎ አድሮ፤ ወያኔን በአደባባይ "ስቀሎ! ስቀሎ!" እንደሚልም አንጠራጠርም።

2ኛ. ወያኔ፤ ግድያን፤ እንደ የብሄራዊ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ መሳሪያ ይጠቀምበታል። በቀልተኝነትንም፤ የፖለቲካው ስልት አድርጎ ይገለገልበታል። ይህ ድርጊት ደግሞ፤ በመርኅ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ አይደለም። ይህ ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ ታፍኖ የቆየው ማኅበራዊ ቅራኔ ውጤት ነው። ወያኔዎቹም፤ በቀልን የመመሪያቸው ማጠንጠኛ አድርገውታል። አማራን ካላጠፉ አይተኙም። በማዋረዳቸው ብቻ አይረኩም። ሌሎችንም እንዲሁ።

3ኛ. ሀገር በዕውቀትና በክኅሎት፤ በተግባርና በምግባር እንጅ፤ በበቀልና በግድያ መምራት አይቻልም። ደርግም ሞክሮ አልተሳካለትም።

4ኛ. አምባገንን ሥርዓት ስለ ራሱ ዕውነትን ለመስማት ጆሮው ስለማይፈልግ፤ ዕውነትን እየሸሻት ይሮጣል። እርሷም እያሳደደች ታጠፋዋለች። የሁለቱን አምባገንነ ሥር ዓቶች ፍፃሜ ያጤኗል! ወያኔም ከዚህ ታሪካዊ የፍርድ ፍፃሜ አያመልጥም።

5ኛ. ሁሉን ቻይና ታዛቢው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፍርድ ቀኑን፤ ጓግቶ ይጠብቃል፤ ያ ቀን መምጣቱ ደግሞ አይቀሬ ነው!

ኢትዮጵያ ሀገራችንም በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች!

ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም!!